# መሥዋዕት ፤

## ኢትዮጵያውያን/ት ፡ ለኢትዮጵያ ፤
## ኢትዮጵያ ፡ ለኢትዮጵያውያን/ት ፤

የካቲት ፡ ፳፩ ፡ ቀን ፡ ፳፻ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፤

## ለኢትዮጵያ ፡ ዓለም ፡ አቀፍ ፡ ሴቶች ፡ በዓል ፤

ክቡራት ፡ እናቶቻችን ፡ እና ፡ እህቶቻችን ፡ ሆይ !

ከሁሉ ፡ አስቀድመን ፡ ክብርት ፡ ሐኪም ፡ ገነትን ፡ እና ፡ በአጠቃላይ ፡ የዜና ፡ አዘጋጅዎች ፡ በየግዜው ፡ እያቀረባችሁ ፡ ለምታስተምሩን ፡ ምስጋና ፡ እናቀርባለን ። ያችን ፡ ዕለት ፡ ለማክበር ፡ እንዲያበቃችሁ ፡ እየተመኘን ፡ ለጥረታችሁም ፡ እናመሰግናለን ። በዜና ፡ ማሰራጫው ፡ የሰማነው ፡ ዕቅዳችሁ ፡ እንዲሳካ ፡ ብርታቱን ፡ ይስጣችሁ ። ክብርት ፡ ወይዘሮ ፡ የሐረር ፡ ወርቅ ፡ ጋሻው ፡ በሚያደርጉት ፡ እንቅስቃሴ ፡ አድንቀናል ። እንደሚቀጥሉበትም ፡ ተስፋ ፡ እናደርጋለን ። ስለሽማግሌ ፡ ያቀረቡትን ፡ ሐሣብ ፡ ነጥቀው ፡ የተጠቀሙበት ፡ አምባገነኖች ፡ ለሕዝብ ፡ መደለያ ፡ ለማድረግ ፡ ነበረ ። ክብርት ፡ የሐረር ፡ ወርቅ ፡ ግን ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሕልውና ፡ ፈላጊ ፡ ስለሆኑ ፡ ስማቸው ፡ መጠቀሱን ፡ አልፈለጉትም ። እንደሚመስለን ፡ አቃለን ፡ እያዩነው ፡ ያለው ፤ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ያለ ፡ መሪ ፡ እና ፡ መንግሥት ፡ ዐሥራ ፡ ሰባት ፡ ዓመታት ፡ እራሱን ፡ በራሱ ፡ እያስተዳደረ ፡ መሆኑን ፡ ነው ። እንደ ፡ ክብርት ፡ ወይዘሮ ፡ የሐረር ፡ ወርቅም ፡ የቀድሞው ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ መንግሥት ፡ ልዩ ፡ መልእክተኛ ፡ የተከበሩት ፡ አቶ ፡ እምሩ ፡ ዘለቀ ፡ ስለሽምግልና ፡ ተጠይቀው ፡ ሲመልሱ ፦ "የውጭ ፡ እጅ ፡ ገብቶበታል" ። ብለው ፡ መለሱ ። በቅርቡም ፡ የሥልጣን ፡ ሽኩቻውን ፡ በመታዘብ ፤ Power struggle for what? በሚል ፡ አብራርተው ፡ ነበረ ። አስተዋይ ፡ እናቶችና ፡ አባቶች ፡ አሉን ። ያጣነው ፡ ግን ፡ አዳምጦ ፡ የሚተገብር ፡ አይምሮ ፡ ነው ። ለዚህም ፡ አንዱ ፡ አምላክ ፡ መፍትሔ ፡ ያምጣልን ። ስለዚህ ፡ ሴት ፡ በመሆኔ ፡ ሐሣቤን ፡ ተቀማሁ ፡ በሚል ፡ ቅርር ፡ አይሰኙ ። ለማለት ፡ ፈልገን ፡ ነው ። ዳግሚያ ፡ መጠቀሚያ ፡ ላለመሆንና ፡ ከሰርጎ ፡ ገቦች ፡ ጥንቃቄ ፡ የምታደርጉትን ፡ ወንዶችም ፡ ልንማረው ፡ ይገባል ።

## የባለሙያ ፡ ኢትዮጵያውያት ፡ ሴቶች ፡ ትውስታ ፣
## ከትናንት ፡ እስተ ፡ ዛሬ ፤

ፈቃድ ፡ ጠይቀንና ፡ አፈላልገን ፡ ያገኘናቸውን ፡ ንሽዎች ፡ ለበዓሉ ፡ ማስታዎሻ ፡ ሊሆኑ ፡ ይችላሉ ፡ የምንላቸውን ፡ አቅርበናል ። እና ፡ ለወደፊቱ ፡ በተሻለ ፡ እንድናቀርብ ፡ አስተያየታችሁን ፡ ልትገጹልን ፡ ትችላላችሁ ።

ደራሲዋ ፣ ግጥም ፡ ገጣሚዋ ፡ እና ፡ የሥዕል ፡ ኪነ ፡ ጠበብቷ ፡ ክብርት ፡ ወይዘሮ ፡ ማርታ ፡ ነሲቡ ፡ ምሥላቸውን ፡ ለበዓሉ ፡ እንድንጠቀምበት ፡ ጠይቀናቸው ፡ ስለፈቀዱልን ፡ ልባዊ ፡ ምስጋናችንን ፡ እንገልጻለን ። አባታቸው ፡ ደጃዝማች ፡ ነሲቡ ፡ ዘአማኔል ፡ የማይጨው ፡ ጦርነት ፡ በምሥራቅ ፡ አዝማች ፡ ሆነው ፡ አገራቸውን ፡ ያገለገሉ ፡ ጀግና ፡ እንደ ፡ ነበሩ ፡ ከታሪክ ፡ መጽሐፍ ፡ አረጋግጠናል ። እኒህ ፡ የሰባ ፡ ስድስት ፡ ዓመታት ፡ የዕድሜም ፡ ባለፀጋ ፡ እና ፡ በለስላሳ ፡ ሙዚቃ ፡ መሣሪያ ፡ ኪነት ፡ ጠበብቷም ፡ የሰማንያ ፡ ዐራት ፡

ዓመታት ፡ ዕድሜም ፡ ባለፀጋ ፡ ጓደኛቸው ፡ እማሆይ ፡ ጽጌ ፡ ማርያም ፡ ገብሩ ፤ ለቀሩት ፡ እናቶቻችንንና ፡ እህቶቻችን ፡ መልካም ፡ አርኣያ ፡ እንደሚሆኑ ፡ አንጠራጠርም ። እጅግ ፡ በጣም ፡ ካስደሰተን ፡ ዜና ፡ ደግሞ ፡ ሁለቱም ፡ የዘመናዊ ፡ ጽሑፍ ፡ መቀመሪያ ፡ ”ኮምፒውተር“ አጠቃቀም ፡ አጥንተው ፡ በመለማመድ ፡ ላይ ፡ ናቸው ። እማሆይ ፡ ”ግዜ ፡ ስለሚያጥረን ፡ ቶሎ ፡ ቶሎ ፡ መማር ፡ አለብን“ ፡ ይላሉ ። ይህ ፡ አባባላቸው ፡ ለኢትዮጵያውያት ፡ እና ፡ ለኢትዮጵያውያን ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ የመመሪያ ፡ መልእክት ፡ አለው ። ስለምንከራባቸውም ፡ ያሰንብትልን ።



እማሆይ ፡ ጽግ ፡ ማርያም ፡ ገብሩ ።

 

ወይዘሮ ፡ ማርታ ፡ ነሲቡ ።

## ለኢትዮጵያ ፡ አገራቸው ፡ ከወንዶቹ ፡ እኩል ፡ የታገሉ ፡ ሴቶች ፤





በሕይወት ፡ እያለን ፡ መተባበር ፡ እና ፡ መረዳዳት ፡ ለሀገርና ፡ ወገን ፡ ጠቃሚ ፡ መሆኑን ፡ የሚስት ፡ አለ ፡ ብለን ፡ አናምንም ። ከዳተኛ ፡ ግን ፡ ሞልቷል ። ሌላው ፡ ድክመታችን ፡ ደግሞ ፡ በሀገር ፡ ልጅ ፡ ላይ ፡ እምነት ፡ ከመጣል ፡ ይልቅ ፡ የውጭ ፡ ዜጋን ፡ አምኖ ፡ ምስጢር ፡ አካፋይነትን ፡ መምረጥ ፡ ነው ። ከሞትን ፡ በኋላም ፡ ያ ፡ ጀግና ፡ እና ፡ ያች ፡ ጀግኒት ፡ ከማለት ፡ በሕይወት ፡ እያለን ፡ መሞከሻሸቱ ፡ ጠቃሚ ፡ ነው ።

# የምጥ ፡ ቀን ፧

አምጠው ፡ ወላጆች ፡ እንደሚረዱልን ፣
በማሰብ ፡ ዕለቱን ፡ ስንለው ፡ የምጥ ፡ ቀን ፣
ግልግሉ ፡ እንዲያምር ፡ ተስፋ ፡ እናደርጋለን ።
ይችን ፡ የሴቶች ፡ ቀን ፡ ስናከብር ፡ ዛሬ ፣
ኅብረት ፡ ዓላማችን ፡ ሊሆን ፡ ጥንካሬ ፣
ቃል ፡ ኪዳን ፡ እንግባ ፡ ያለ ፡ ጥርጣሬ ።
        ፈጣሪ ፡ በማቀድ ፡ ሲዘጋጅ ፡ ለሥራው ፣
        ወንድን ፡ ቀድሞ ፡ ፈጥሮ ፡ አጋሩን ፡ ሲሰጠው ፣
        ሴት ፡ ብሎ ፡ ሰይሞ ፡ ተባዝተህ ፡ ኑር ፡ ሲለው ፣
        የጎደለው ፡ ጎኑ ፡ እንዲሟላለት ፡ ነው ።
የእግዜር ፡ በኩር ፡ አገር ፡ ኢትዮጵያ ፡ እናታችን ፣
በርቱ ፡ ጠንክሩ ፡ በይ ፡ ሴቶች ፡ ልጆችሽን ።
ጡትሽን ፡ አጥብተሽ ፡ በማሳደግሽ ፣
ፈትፍተሽ ፡ አጉርሰሽ ፡ በመመገብሽ ፣
ጡትና ፡ ጣቶችሽን ፡ የመነከስሽ ፣
ቁስልና ፡ መግሉ ፡ ሲነዘንዙሽ ፣
ያላዘነ ፡ የለም ፡ ምሕረቱን ፡ ይስጥሽ ።
ያም ፡ አልፏል ፡ ዓይተሻል ፡ ይኸም ፡ ያልፋልና ፣
ምንግዜም ፡ አምላክሽ ፡ አይረሳሽምና ፣
ጸሎትሽ ፡ ሰምሮልሽ ፡ እንይሽ ፡ በጤና ።
        እንደ ፡ እናት ፡ ራሪ ፣
        እንደ ፡ እህት ፡ አክባሪ ፣
        እንደ ፡ ወንድ ፡ አቅራሪ ፣
        እንደ ፡ ሴት ፡ መካሪ ፣
        በዘዴኛ ፡ ስልትሽ ፡ ሰላምን ፡ አብሳሪ ፣
        እንደነ ፡ ዘራፌ ፡ ወንድም ፡ አዳፋሪ ።
አሁንም ፡ አንቺው ፡ ነሽ ፡ ኩሪ ፡ እናታችን ፣
ወደፊት ፡ ቀጣይት ፡ በርቺ ፡ እህታችን ።
ሴት ፡ የሌለው ፡ አገር ፡ ሥልጣኑ ፡ አይበረክት ፣
አይሆንም ፡ ካላንቺ ፡ ሰምተነዋል ፡ ከጥንት ።
ወላጆች ፡ ስታውቁ ፡ አርግዞ ፡ ማማጥ ፣
ይህንን ፡ የምጥ ፡ ቀን ፡ ገላግሉት ፡ በቅጥ ፣
ዘዴ ፡ አላችሁና ፡ ልጅ ፡ ወልዶ ፡ ማስሮጥ ።
ስለዚህ ፡ የምጥ ፡ ቀን ፡ አዋላጅ ፡ ስላሉን ፣
አስታማሚ ፡ ሐኪሞች ፡ እህቶቻችን ፣
ሰላም ፡ ተወልዶልን ፡ ማየት ፡ እንሻለን ።

## ድል ፡ ለኢትዮጵያና ፡ ሕዝቧ ።

**ስለሺነህ ፡ ገላነህ ፣**
**ተጠሪ ።**
E-mail: sileshineh@yahoo.com